# መቼም ቢሆን የማይቀለበስ አቋም

**ወንድይራድ ኃብተየስ** 08-29-17

"ህገ መንግሥቱ የህዝቦቻችን የዘመናት ትግል ውጤት ነው፤ ይህን የህዝቦቻችንን የዘመናት ትግል ግምት ውስጥ በማስገባት ነው ህገ መንግሥቱ የተረቀቀው። የኢትዮጵያ ባህል ማለት የኢትዮጵያ ህዝቦች ባህሎች ተደምረው የሚፈጥሩት ነው። የኢትዮጵያ ቋንቋ ማለት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በሙሉ ተደምረው የሚፈጥሩት ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የህዝቦች ታሪክ ተደምሮ የሚፈጥረው ነገር ነው። ይህ ታሪክም በልዩነት የሚስተናገደው በፌዴራሊዝም ሥርዓት ነው" ብለው ነበር ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት። እናም ለአገሪቱ ብቸኛው አማራጭ ፌዴራላዊ ሥርዓትን መከተል እንደሆነም ጨምረው ገልፀዋል።

እርግጥ ነው። ይህንን የታላቁን መሪ አባባል በአገራችን በተጨባጭ እውን ሲሆን አይተነዋል። ከእርሳቸው ህልፈተ ህይወት በኋላም ቢሆን ሥርዓቱ ፈሩን ሳይስት ቀጥሏል። ምንም እንኳን ከህልፈታቸው በኋላ አንዳንድ ፅንፈኞች 'አገሪቱ ባልተረጋጋ ውስጣዊ የፖለቲካ ችግር ትናጋለች፣ ህዝቦቿም እርስ በርሳቸው ይባላሉ…ወዘተ' የሚሉ መጥፎ ሟርት ሰንቀው ቢዋትቱም። ዳሩ ምን ያደርጋል! ለዚህ የሴራ አቋማቸው ማንም ጆሮ አልሰጠውም። ምክንያቱም የፌዴራል ሥርዓቱ ፅንፈኞቹ የሚሉትን ዓይነት በድንቡሽት ላይ የተገነባ ቤት አይደለምና። ይልቁንም በህዝቦች መፈቃቀድና በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ በመሆኑ ጭምር ይዘውት ለተነሱት ሀሳብ ሊያፍሩበት በተገባ።

"ስለ ኢፌዴሪ ህገ መንግሥት አንዳንድ ማብራሪያዎች" በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ዶክተር ሐሺም ቶውፊቅ የተባሉ ሙያተኛ በ1999 ዓ.ም ላሪያ ዳይመንድ የተባለ የውጭ ፀሐፊን በመጥቀስ እንዲህ ብለው ነበር። "ፌዴራሊዝም በማህበራዊ ምንነት ምክንያት የሚፈጠር ልዩነቶችን ለማቻቻል ወይም አብሮ ለማራመድ እና በማህበራዊ ምንነት ወይም በሌላ የማንነት ልዩነቶችን መሠረት ያደረጉ ግጭቶችን ለማስተንፈስ አግባብነት ያለው የፖለቲካ መሣሪያ ነው" የሚል። ይህ አብሮነትም ዜጎች የጋራ ምጣኔ ሀብታቸውን ለማሳደግ ሥርዓቱ የጎላ ሚና እንደሚጫወት አብራርተዋል። ይህን እውነታ የተገነዘበው የአገራችን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግሥትም ህገ መንግሥቱን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በገዛ ፈቃዳቸው ተስማምተው እና ተማምነው እንዲያፀድቁት የተጫወተው ሚና በእጅጉ የላቀ ነው። ይህችን አገር ከአምባገነኑ የደርግ ሥርዓት አገዛዝ ያላቀቀው ኢሕአዴግ የአገሪቱ ህዝቦች ትግል፤ ሥልጣን በህዝብ እና በህዝብ ብቻ የሚረጋገጥ እንደሆነም የሚያምን ነው። በመሆኑም በዚህ የአገሪቱ የበላይ ህግ ህዝቦች የትግላቸው ባለቤት እንዲሆኑ ችለዋል።

እነዚህ ጽንፈኞች የታላቁ መሪ መለስ ዜናዊን ድንገተኛ የዜና እረፍት ተከትሎ ያልቀባጠሩት የወሬ ዓይነት አልነበረም። የእነርሱ የወሬ ማራገቢያ የሆኑት ሚዲያዎችን በመጠቀምም፤ 'ኢትዮጵያ ከድህረ መለስ በኋላ የተረጋጋ መንግሥት አይኖራትም' የሚል ትንቢት መሳይ ቅጥፈትን ማስታወስ ይቻላል። እርግጥ እነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎች በዜሮ ድምር የፖለቲካ ስሌት የሚመሩ በመሆናቸው ይጠቅመናል ብለው ካሰቡ ምንም ነገር ከማለት ወደ ኋላ የሚሉ አይደሉም። አሁን ከድህረ መለስ በኋላ እነርሱ የተመኟት ኢትዮጵያ 'አለች ወይ?' ብለው እንኳን የማይጠይቁ የጨለማ ታንኳ ቀዛፊዎች ናቸው። አዎ! የእነርሱ በከሰረ የፖለቲካ እሳቤያቸው የሚያራምዱት 'የአገር ትበታተናለች' የወረደ ትንታኔ ከእነሱ ውጪ ማንንም ሊያሳምን አይችልም። ለዚህም አብነቶችን እንጠቃቅስ።

የዛሬ አምስት ዓመት በታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ ደንገተኛ ሞት ያልደነገጠ ኢትዮጵያዊ እና የኢትዮጵያ ወዳጅ ህዝብ አልነበረም። ህዝቡ ለመሪው የነበረውን ጥልቅ ፍቅር በይፋ አስከሬናቸው ከውጭ አገር በመጣበት ጊዜ የወቅቱ ዝናብ እና ብርድ ሳይበግረው ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ጀምሮ ቤተ መንግስት ድረስ አጅቧል። ጥልቅ ሀዘኑንም ለሁለት ሣምንታት ያህል ከአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን፤ ከክልሎችና ከውጭ አገር ጭምር በመሰባሰብ ሃዘኑን ገልጿል። ፅንፈኞቹ ግን ይህን አይተው ሲያበቁ መለስን የሚተኩ እልፍ አዕላፍ መለሶች እንዳልፈጠሩ ሁሉ አገሪቱ አበቃላት ሲሉ ቢያሟርቱም ህዝቡ ግን ጆሮውን አልሰጣቸውም።

በእርግጥ የታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ ህልፈተ - ህይወት ጥልቅ ሃዘንን እና ድንጋጤን የፈጠረ ነበር። ነገር ግን ህዝቡ ከጫፍ እስከ ጫፍ ታላቁ መሪያችን በቀየሱልን የፌዴራላዊ ሥርዓት መንገድ ተከትለን አንድነታችንን በማጠናከር በእልህ እና በወኔ ራዕይህን እናሳካለዋለን ብሏል። በርካታ የውጭ መገናኛ ብዙሃንም ከፅንፈኞቹ በተፃራሪ ህዝቡ ለመሪው ያደረገው የቀብር ሥነ ሥርዓት አስገርሟቸው ‘ኢትዮጵያዊያን የሚወዳቸውን መሪያቸው በክብር ቀበሩ’ ሲሉ ዘግበዋል። የውጭ መገናኛ ብዙሃን እንዲህ ሲሉ የአገራችን ተቃዋሚ ተብዬዎችና ፅንፈኛ ኃይሎች ግን የገዛ አገራቸውን ለብተና መመኘታቸው በህዝቡ ዘንድ ከትዝብት ውጪ ያተረፈላቸው አንዳችም ነገር የለም። የአገራችን ፌዴራላዊ ሥርዓት የከሸፈ መሆኑን በሚያስገርም ሁኔታ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ጥቃቅን ኑባሬያዊ ሰበዞችን እያጋነኑ በመምዘዝ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎቹ በጭፍን ሊከራከሩ ሲሞክሩ ይስተዋላሉ። እናም በዚህ በሚያስገርም ጨለምተኛ እሳቤያቸው ዓለም የመሰከረውን ዕድገት ያመጣው ፌዴራላዊ ሥርዓት ከሽፏል ሲሉ አፋቸውን አይዛቸውም።

እኚህ በጨለማ ውስጥ የሌለን ነባራዊ ሁኔታ እየተነተኑ አፈ ታሪክ የሚያንበለብሉ ፅንፈኞች በየትኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ ግጭት መቼም ቢሆን ሊጠፋ የማይችል ነባራዊ ሁኔታ መሆኑን አያውቁም ወይም ቢያውቁም ለመናገር የሚደፍሩ አይደሉም። ምክንያቱም ለእነርሱ ጥላሸት የመቀባት ሥራ ይህ ሃቅ ምንም ስለማይጠቅማቸው ነው። ሆኖም እንኳንስ የህዝቦች ንቃተ ህሊና እየተገነባ እና ይበል የሚያሰኝ ደረጃ ላይ እየደረሰ ባለበት በእኛ አገር ውስጥ ቀርቶ በሥልጣኔ እጅግ በዳበሩ ሌሎች አገሮች ውስጥም ቢሆን ግጭት መኖሩ አይቀርም። ሰው ከራሱ፣ በአቅራቢያው ካለውና ከተፈጥሮ ጋር መጋጨቱ አይቀሬ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በዓለማችን ላይ ያለው የተፈጥሮ ሃብት እጥረት ነው። ኢትዮጵያም ከዚህ የተለየች አይደለችም — እንደ ማንኛውም የዓለማችን ክፍል የተፈጥሮ ሃብት እጥረት አለባት። እናም ግጭት ትናንትም ይሁን ዛሬ መኖሩ ያለና የሚኖር ጉዳይ ነው።

ሆኖም ፌዴራላዊ ሥርዓቱ ካለፉት ጊዜያት ጋር ፈፅሞ በማይገናኝ መልኩ ለዚህ ነባራዊ ችግር ትኩረት ሰጥቶ በመሥራቱ ሁኔታውን በመለወጥ ላይ ይገኛል። የአገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ያላቸውን የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ እንዲጠቀሙና ከሌሎች ህዝቦች ጋር በመተሳሰብ የጋራ ሃብታቸው እንዲሆን ማድረግ ችሏል። ዳሩ ግን ያለፉት ሥርዓቶች በአገራችን ህዝቦች ውስጥ ፈጥረውት ያለፉት የተዛቡ አመለካከቶች እንዲህ በቀላሉ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በዋዛ የሚቀየሩ አይደሉም — ሂደትን፣ ጊዜንና የአስተሳሰብ ለውጥን ይጠይቃሉ። እናም ይህን ሃቅ ወደ ጎን ገሸሽ አድርጎ ሥርዓቱን ጥላሸት ለመቀባት ካላቸው ፍላጎት ብቻ በመነሳት ‘የከሸፈ ፌዴራሊዝም’ መሆኑን ያለ አንዳች ሃፍረት ሊነግሩን ይሞክራሉ። ግና በሚያስገርም ሁኔታ እንደሚሉት የፌዴራል ሥርዓቱ አልከሸፈም። ይልቁንም ሥርዓቱ የአገሪቱን ህዝቦች በአንድነት በማስተሳሰር ከሰሃራ በታች ጠንካራ ምጣኔ ሃብት መገንባት የቻለና ህዝቡንም በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረገ ሆኗል። ስለሆነም የፅንፈኞች ‘የክሽፈት ዓለም’ ምኞት ምናብ ውስጥ እንጂ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ውስጥ የሌለ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል ባይ ነኝ። ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ይልቅ

በፈረንጆችና የራሳቸው እኩይ አጀንዳ ባላቸው ግለሰቦች አባባሎች የሚያምኑትና እነዚያን ሽውራራ ዕይታዎች እንደወረዱ የሚያቀርቧቸው ፅንፈኞች የፌዴራል ሥርዓቱ ክሽፈት ማሣያ መሆኑን ሲናገሩ ከእውነታው በአያሌው ማፈንገጣቸውን ከመጤፍ አልቆጠሩትም።

ያም ሆነ ይህ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተገነባ ያለው ሥርዓት ራሱን በራሱ እያረመና እያስተካከለ የሚሄድ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። እንደሚታወቀው ማንኛውም ፌዴራላዊ ሥርዓት በአንድ ጀምበር የተገነባ አይደለም። ተግዳሮቶች መኖራቸው አይቀርም። እናም በሂደቱ ውስጥ ጥቃቅን ስንክሳሮች ሊያጋጥሙት ይችላል። ዋናው ነገር እነዚህ ጊዜያዊ ችግሮች በብቃት እየተፈቱ የመሄዳቸው ጉዳይ ነው። ከዚህ አኳያ በአገራችን በመገንባት ላይ ያለው ፌዴራላዊ ሥርዓት ለሚፈጠሩ ሁነቶች ወቅታዊና አስተማማኝ ምላሽ እየሰጠ ዛሬ ላይ ደርሷል። በዚህም ሊፈጠሩ የሚችሉ አነስተኛ ኑባሬያዊ ተግዳሮቶችን በመፍታት ሁሉም የአገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በጋራ ተሳስበውና ተፈቃቅደው የሚኖሩበትን አስተማማኝ ሥርዓት መፍጠር ተችሏል። ከዚህ ውጪ ፅንፈኞች በጨለምተኛ እሳቤያቸው እንደለመዱት ‘እነ እገሌ እንዲህ ስለሆኑ ፌዴራላዊ ሥርዓቱ ከሽፏል’ ማለታቸው የሚያነሱት ሃሳብ እጥረት ያለባቸው መሆኑን ከማሳበቅ በስተቀር ሌላ ፋይዳ የለውም። ነገርዬው ግን አስቂኝ ነው። ሥርዓቱን ቅዠት በወለደው ምናባቸው ካከሸፉት አሁን ያለው ሥርዓት ከቶ ምን ይሆን?

እዚህ ላይ አንድ እውነታን እናንሳ። የኢትዮጵያ ህዝቦች የታገሉለትንና በህገ መንግሥቱ ውስጥ ተካትቶ ዛሬም ሆነ ነገ በፅናት የሚያምኑበትን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የማይገሰሱ መብቶች ላይ ከቶም ቢሆን እንደማይደራደሩ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ የአገራችን ህዝቦች ያላቸው አቋም መቼም ቢሆን እንደማይቀለበስ ነው።